22 ፱

ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን
ቤተ መጻሕፍት
Library

# የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን
# የስታቲስቲክስ ጥሬ መረጃ አሰጣጥ መመሪያ

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን
ግንቦት 1996
አዲስ አበባ

# የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን
# የስታቲስቲክስ ጥሬ መረጃ አሰጣጥ መመሪያ

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን
ግንቦት 1996
አዲስ አበባ

13/03/97

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን
ቤተ መጻሕፍት
C. S. A. Library

# የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን

# የስታቲስቲክስ ጥሬ መረጃ አሰጣጥ መመሪያ

## አስፈላጊነት

- ባለሥልጣን መ/ቤቱ በኢኮኖሚና በማህበራዊ ዘርፎች የሰበሰባቸውን መረጃዎች አጠናቅሮና ተንትኖ እስካሁን በአብዛኛው የሚያቀርበው የሪፖርት ውጤቶችን /Publications/ ሲሆን ከዚህ በበለጠ ዝርዝር መረጃዎችን በተጠቃሚዎች ፍላጎት ላይ ተመስርቶ ለማቅረብ እንዲያስችለው፣

- ባለሥልጣን መ/ቤቱ ቀደም ሲል ጥናቶችን በገንዘብና በማቴሪያል ለሚረዱና ለከፍተኛ የፖሊሲ አውጪ መንግስታዊ ድርጅቶች ጥሬ መረጃ ካለክፍያ ሲሰጥ የቆዬ ቢሆንም ሁሉን አቀፍ የሆነ በሕግና በደንብ መሠረት የሚመራና ወጥነት ያለው መመሪያ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

- ጠለቅ ያለ ጥናትና ምርምር ለማድረግ ጥሬ መረጃዎችን ወይም ተጨማሪ ዝርዝር መረጃዎችን መረጃ ተጠቃሚዎች ወጪውን እንዲጋሩ በማድረግ ማቅረብ በማስፈለጉ፣

- ጥሬ መረጃዎችን ወይም ባለሥልጣን መ/ቤቱ ከሰበሰባቸው መረጃዎች ውስጥ በዝርዝር የማይወጡትን በበለጠ ዝርዝር ለማግኘት ለሚፈልጉ ወጥነት ባለው መንገድ ለማስተናገድ እንዲቻል፣

- ባለሥልጣን መ/ቤቱ የሰበሰባቸውን መረጃዎች የተጠቃለሉና የተንተኑ መረጃዎችንም ቢሆን ውጤቱን በሪፖርት /Publication/ መልክ ብቻ ሳይሆን በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎች አማካይነት ለማቅረብ የሚያስፈልገውን ቅድመ ሁኔታ እያሟላና አቅም እየገነባ በመሆኑ፣ የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣንን ተግባርና ኃላፊነት ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 303/1964 መሠረት ይህ የስታቲስቲክስ ጥሬ መረጃ አሰጣጥ መመሪያ ወጥቷል።

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን
ቤተ መጻሕፍት
C. S. A. Library

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን የስታቲስቲክስ ጥሬ መረጃ አሰጣጥ መመሪያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይቻላል።

### 2. ትርጓሜ፣

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፣

2.1 "ጥሬ መረጃ" ማለት ኮድ የተደረገም ሆነ ያልተደረገ በድርጅት፣ በቤተሰብ ወይም በግለሰብ ደረጃ ያለ ያልተጠቃለለ ወይም ያልተቀነባበረ የቆጠራ ቦታ፣ ቀበሌ/ገበሬ ማህበር፣ ወረዳ፣ ዞን፣ ክልል ወይም አገር አቀፍ መረጃ ነው።

2.2 "ባለሥልጣን መ/ቤት" ማለት የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ነው።

2.3 "ቆጠራ/ሴንሰስ/" ማለት ወሰኑ በውል በታወቀና በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ ስለሕዝብ፣ ቤት፣ ግብርና፣ ኢንዱስትሪ፣ ንግድ፣ እና የመሳሰሉ ዘርፎች ላይ የሚደረግ አጠቃላይ /ሙሉውን የሚሸፍን/ ቆጠራን በማካሄድ መሠረታዊ መረጃዎችን የመሰብሰብ፣ የማጠናቀር፣ የመገምገምና ውጤቱንም ለተጠቃሚዎች የማሠራጨት ተግባር ነው።

2.4 "የናሙና ጥናት" ማለት መረጃ ከሚፈለግበት ከጠቅላላው ውስጥ በከፊል ወይም የሚያስፈልገውን ያህል በመምረጥ የሚካሄድ የሕዝብ፣ የማህበራዊ፣ የቤት፣ የግብርና፣ የኢንዱስትሪ፣ የንግድ፣ የቤተሰብ በጀትና የዋጋዎች.... ወዘተ በሚመለከት ወካይ የሆኑ መረጃዎች የመሰብሰብና በዚሁም መሠረት የማጠናቀር፣ የመገምገምና ውጤቱንም ለተጠቃሚዎች ማሠራጨት ነው።

2.5 "አስተዳደራዊ መዛግብት" ማለት የተለያዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በዕለት ተዕለት የአስተዳደር ሥራቸው የሚመነጩ መረጃዎችን የማጠናቀርና የማቀነባበር ተግባር ነው፡፡

2.6 አገር አቀፍ መረጃ ማለት አገር አቀፍ ከተማ፣ አገር አቀፍ ገጠር ወይም ጠቅላላው ሊሆን ይችላል፡፡

2.7 "ለጥናቱ የተዘጋጀው በጀት" ማለት መረጃውን ለመሰብሰብና ለማቀነባበር የተያዘ የካፒታል በጀት ነው፡፡

2.8 " ዝቅተኛ የሪፖርት ደረጃ" ማለት ጥናቱ ተቀነባብሮ ውጤቱ የሚወጣበት የአስተዳደር እርከን /ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፣ ቀበሌ/ገበሬ ማህበር/ ነው፡፡

2.9 "የጥናቱ የተወሰነ ክፍል (limited variables)" ማለት ለአንድ ጥናት ከተሰበሰቡት የመረጃ ዓይነቶች ውስጥ ከፊል መረጃውን ብቻ የሚያመለክት ነው፡፡

2.10 "የጥሬ መረጃ መጠየቂያ ቅጽ" ማለት የጥሬ መረጃውን የሚፈልገው ግለሰብ/ድርጅት የሚፈልገውን ጥሬ መረጃ ዓይነትና መረጃው የተፈለገበትን ምክንያትና አጠቃቀሙን በመግለጽ ዝርዝር መብቶችና ግዴታዎችን በማወቅ ስለአፈጻጸሙ የሚሞላው ቅጽ ነው፡፡

2.11 "ቀበሌ" ማለት በየወረዳው ስር የሚገኝ በአገሪቱ የመጨረሻው አስተዳደር እርከን ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

## የጥሬ መረጃ አሰጣጥ

### 3. ጥሬ መረጃ የሚሰጥባቸው ሁኔታዎች፣

3.1 ጥሬ መረጃ የሚሰጠው ባለሥልጣን መ/ቤቱ የመጀመሪያ ምንጭ ለሚሆንባቸው በናሙና ጥናት/Sample Survey/ እና በአጠቃላይ ቆጠራ /Census/ ለተገኙ መረጃዎች ይሆናል፡፡

የናሙና ጥናትና አጠቃላይ ቆጠራ ሲባል፣

3.1.1 ቤተሰብን /Household survey approach/ ፣

3.1.2 የኢኮኖሚና ማህበራዊ ድርጅቶችን /Establishment survey approach/ መሠረት በማድረግና መጠይቅ በመጠቀም የሚሰበሰቡ መረጃዎችን ያጠቃልላል፡፡

3.2 ጥሬ መረጃ የሚሰጠው የግለሰቦችን፣ የቤተሰቦችን ወይም የድርጅቶችን ማንነት በማያሳይ መልኩ መሆን አለበት፡፡

3.3 ጥሬ መረጃ የሚሰጠው ባለሥልጣን መ/ቤቱ የሰበሰባቸውን ጥሬ መረጃዎች አጠናቅሮና ተንትኖ በሪፖርት መልክ ካሠራጨ በኋላ መሆን አለበት፡፡

3.4 ከላይ በተራ ቁጥር 3.2 የተደነገገው ቢኖርም ጥሬ መረጃ የተጠየቀበትን ጥናት በቴክኒክ፣ በፋይናንስና በማቴሪያል ለረዱ ድርጅቶች/ተቋሚት /በተለይም በሪፖርት ዝግጅት ላይ አብረው የሚሳተፉ ከሆነና ሪፖርቱን ለማዘጋጀት ጥሬ መረጃው ካስፈለገ/ የጥናቱ ሪፖርት ከመሠራጨቱ በፊት እንዲሰጣቸው ሊደረግ ይችላል፡፡

3.5 አጠቃላይ ቆጠራን በሚመለከት በተለይ ለትላልቅ ቆጠራዎች ጥሬ መረጃ ሊሰጥ የሚችለው ከጠቅላላው ከተሰበሰበው መረጃ ከ1-10 በመቶ ላልበለጠ መረጃ ብቻ ይሆናል፡፡

3.6 ከላይ በተራ ቁጥር 3.4 የተደነገገው ቢኖርም በቀበሌ ደረጃ የተጠየቀ የአጠቃላይ ቆጠራ ጥሬ መረጃ በከፊል ሳይሆን ሙሉ በሙሉ እንዲሰጥ ሊደረግ ይቻላል፡፡

## 4. የጥሬ መረጃ በነፃ የሚሰጣቸው አካላት

4.1 ለፖሊሲ አውጪ መንግሥታዊ አካላት/ድርጅቶች፣

4.2 በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከመጀመሪያ ዲግሪና በላይ በመማር ላይ ላሉ፣

4.3 ጥሬ መረጃ የጠዩቀበትን ጥናት በፋይናንስና በቴክኒክ ለረዱ ድርጅቶች/ተቋማት፣

## 5. የስታቲስቲክስ ጥሬ መረጃ ሊሰጣቸው የማይገባ አካላት፣

5.1 ስለ መረጃው አጠቃቀም የተቀመጠውን ቅድመ ሁኔታ ለማሟላት ግዴታ ለመግባት ፈቃደኛ ላልሆኑ አካላት፣

5.2 ከስታቲስቲክስ መረጃ አጠቃቀም ስነ-ምግባር ውጪ አንድ መረጃ ጠያቂ ጥሬ መረጃውን ይጠቀምበታል የሚል ጠቋሚ መረጃ ካለ፣

5.3 የአንዳንድ ቆጠራዎችና ጥናቶች ጥሬ መረጃዎች ከትልቅነታቸው እና/ወይም ከአጠቃቀም ላይ ሊደረግ ከሚገባው የተለየ ጥንቃቄ ጋር ተገናዝቦ የእዚያ ጥናት ጥሬ መረጃ መስጠት እንደሌለበት በሥራ ክፍል ኃላፊዎች በተጨባጭ ማስረጃ ተረጋግጦ ከቀረበ፣

## 6. የጥሬ መረጃ ጠያቂዎች ግዴታ

6.1 ጥሬ መረጃው የተፈለገበትን ምክንያትና አጠቃቀሙን የሚያብራራ ፕሮፖዛል በጽሑፍ ገልጾ የማቅረብ፣

6.2 ጥናቱ ከሚፈቅደው ዝቅተኛ የሪፖርት ደረጃ በታች መረጃውን ላለማጠናቀር፣

6.3 የወሰዱትን ጥሬ መረጃ በሽያጭ ወይም በነፃ ለሦስተኛ ወገን አሳልፎ ላለመስጠት፣

6.4 የግለሰቦችን /የቤተሰቦችን / የድርጅቶችን ምንነት በሚያሳይ መልኩ መረጃውን ላለመጠቀም፣

6.5 በነፃ ጥሬ መረጃ እንዲያገኙ የተፈቀደላቸው የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎችና ተመራማሪዎች የጥናት ውጤታቸውን አንድ ኮፒ ለባለሥልጣን መ/ቤቱ ለመስጠት፣ ግዴታ መግባት ይኖርባቸዋል።

## 7. የጥሬ መረጃ አሰጣጥ የአፈጻጸም ስልቶች፣

7.1 የባለሥልጣን መ/ቤቱ የመረጃ ማቀነባበሪያ መምሪያ አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት በማድረግ መረጃውን በኮምፒዩተር ከማደራጀት በተጨማሪ የየጥናቶችን የጥሬ መረጃ ዝርዝር መግለጫ /ዳታ ዲክሽነሪ፣ የአጠቃቀም

መግለጫና መጠይቅ/ ጭምር በኮምፒዩተር በመያዝ ቀልጣፋና ብቁ የሆነ አገልግሎት ይሰጣል።

7.2 የስታቲስቲክስ ጥሬ መረጃ የሚሰጠው በሕዝብ ግንኙነት አገልግሎት በኩል የጥሬ መረጃ መጠየቂያ ቅጽ ተሞልቶና በሚመለከታቸው አካላት ተፈቅዶ ለመረጃ ማቀነባበሪያ መምሪያ ሲቀርብ ይሆናል።

7.3 የጥሬ መረጃ በነጻ እንዲያገኙ ከተመለከቱት አካላት በስተቀር የስታቲስቲክስ ጥሬ መረጃ ለማግኘት የሚጠይቁ ሌሎች አካላት በሚኒስትሮች ም/ቤት ደክፍያ ተመን መሠረት ይሰጣቸዋል።

## ክፍል ሦስት

## የስታቲስቲክስ ጥሬ መረጃ የክፍያ አወሳሰንና ተመን

### 8. የጥሬ መረጃ የክፍያ አወሳሰን

8..1 የጥሬ መረጃ ለእያንዳንዱ ቆጠራና የናሙና ጥናት ውጤት የሚሰጠው ሚያዚያ 15 ቀን 1996 በሚ/ሮች ምክር ቤት በተወሰነው የክፍያ ተመን መሠረት ቀጥሎ በቀረበው ሠንጠረዥ ላይ እንደተመለከተው ይሆናል።

8..2 በክልል፣ በዞን፣ በወረዳና የጥናቱን የተወሰነ ክፍል /Limited Variables/ አስመልክቶ ለሚጠየቁ ጥሬ መረጃዎች የአንድ ዝቅተኛ የሪፖርት ደረጃ ተመን በዚህ መመሪያ ተራ ቁጥር 8.4 ውስጥ የተመለከተ ሲሆን ከአንድ ዝቅተኛ የሪፖርት ደረጃ በላይ ለሚጠይቁ የአንዱን ተመን በሚፈልጓቸው የዝቅተኛ የሪፖርት ደረጃዎች ብዛት ጋር በማባዛት ይገኛል።

| ተ.ቁ | ለጥናቱ የተያዘው በጀት | የክፍያ ተመን ዲስኬቶችን ጨምሮ |
|---|---|---|
| | **8.3 ለአገር አቀፍ መረጃ፣** | |
| ሀ | ከአምስት ሚሊዮን ብር በታች | 7,550 ብር |
| ለ | አምስት ሚሊዮን ብር እና በላይ | 15,100 ብር |
| | **8.4 አንድን ዝቅተኛ የሪፖርት ደረጃ ወይም የተወሰነ የጥናቱን ክፍል አስመልክቶ ለሚፈለግ መረጃ** | |
| ሀ | ከአምስት ሚሊዮን ብር በታች | 550 ብር |
| ለ | አምስት ሚሊዮን ብር እና በላይ | 1,100 ብር |

8..5 የተቀነባበሩ የጥናት ውጤቶች በተለያዩ ኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎች እንዲሰጣቸው ለሚጠይቁ አካላት፣

8..5.1 እስከ 100 ገጽ ላላቸው የጥናት ሪፖርቶች ብር 40፣

8..5.2 ከ101 እስከ 400 ገጽ ያላቸው ከሆነ ብር 80፣

8..5.3 ከ400 ገጽ በላይ ያላቸው ከሆነ ብር 100 በመክፈል መረጃውን እንዲያገኙ ይደረጋል።

## 9. መመሪያውን ስለማሻሻል

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ይህን መመሪያ በየጊዜው እየገመገመ በጥናት ላይ የተመሠረተ ማሻሻያ ማድረግ ይችላል።

## 10. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከግንቦት 1 ቀን 1996 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን

## የስታቲስቲክስ ጥሬ መረጃ /Raw Data/ መጠየቂያ ቅጽ

1. የጠያቂው ድርጅት/ግለሰብ ስም ____________________

2. ጥሬ መረጃ ጠያቂው፡- የመንግሥት መ/ቤት ☐ የምርምር ተቋም ☐
የከፍተኛ ት/ተቋም ☐ ተመራማሪ ☐ የዩኒቨርስቲ ተማሪ ☐
ለተጠየቀው ጥናት ድጋፍ ያደረገ ድርጅት ☐ የግል/የኮንስልታንት ድርጅት ☐
መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ☐ የውጪ ድርጅት ☐ ሌላ ☐ ____________________

3. የሚፈለገው መረጃ የተሰበሰበበት የቆጠራ ወይም የናሙና ጥናቱ
ስም ____________________

4. መረጃው የሚመለከተው፣ አገር አቀፍ ☐ ክልል ☐
ዞን ☐ ____________ ወረዳ ☐ ____________
ቀበሌ ☐ ____________ ሌላ ☐ ____________

5. መረጃው የተፈለገበት ምክንያትና የአጠቃቀሙ ፕሮፖዛል በአጭሩ ይገለጽ
________________________________________
________________________________________

6. የሥራ ክፍሉ ኃላፊ አስተያየትና ፊርማ
________________________________________

7. የፈቀደው ባለሥልጣን፡- መረጃው በነፃ ☐ በክፍያ ☐ ይሰጣቸው።
ፊርማ ____________________

8. ጥሬ መረጃው የሚሰጠው በክፍያ ከሆነ አጠቃላይ ቆጠራውን ወይም ናሙና ጥናቱን ለማካሄድ የተመደበ በጀት በብር ____________________

9. የሕዝብ ግንኙነት አገልግሎት ኃላፊ፡- በክፍያ ከሆነ ብር ______________
ከፍለው ይሰጣቸው፤ ፊርማ ______________

10. መረጃው የተሰጠበት ቀንና ዓ.ም ______________

11. <u>የመረጃ ጠያቂው ግዴታ</u>፣

11.1 የወሰድኩትን መረጃ በሽያጭ ወይም በነፃ ለሦስተኛ ወገን አሳልፌ ላለመስጠት፣

11.2 የግለሰቦችን/የቤተሰቦችን/የድርጅቶችን ማንነት በሚያሳይ መልኩ መረጃውን ላለመጠቀም

11.3 በነጻ ጥሬ መረጃ እንዲያገኙ የተፈቀደላቸው የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎችና ተመራማሪዎች የጥናት ውጤታቸውን አንድ ኮፒ ለባለሥልጣን መ/ቤቱ ለመስጠት፣

11.4 ጥናቱ ከሚፈቀደው የሪፖርት ደረጃ በታች መረጃውን ላለማጠናቀር ግዴታ የገባሁ ሲሆን፣

11.5 ከተራ ቁጥር 11.1-11.4 የተገለጹትን ግዴታዎች ተላልፌ ብገኝ በ1949 ዓ.ም በወጣው አግባብ ባለው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ እንዲሁም የስታቲስቲክስ ጠቅላይ ጽ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው ትዕዛዝ ቁጥር 79/64 እና አዋጅ ቁጥር 303/64 በተጠቀሰው የሕግ አንቀጽ መሠረት ተገቢው ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድብኝ ተስማምቼ ፊርሜአለሁ።

12. <u>የእማኞች ስምና ፊርማ</u>

12.1 ______________

12.2 ______________

12.3 ______________

13. የመረጃ ጠያቂው ስምና ፊርማ ______________
ቀን ______________

# MINISTRY OF FINANCE AND ECONOMIC DEVELOPMENT
# CENTRAL STATISTICAL AUTHORITY

## DIRECTIVE ISSUED TO ESTABLISH PROCEDURES FOR ACCESSING RAW DATA TO USERS

CENTRAL STATISTICAL AUTHORITY

MAY, 2004

ADDIS ABABA

# DIRECTIVE No. 1 /2004

# DIRECTIVE ISSUED TO ESTABLISH PROCEDURES FOR ACCESSING RAW DATA TO USERS

- Whereas, the Authority has been collecting socio-economic data and thereby processing, analyzing, preparing and publishing the reports, and have been accessing to users, however, in order to enable the Authority to access these data on the basis of the demand of the users and in a more comprehensive manner;
- Whereas, the Authority has been and is accessing raw data free of charge to government agencies, researchers in higher educational institutions, and to donors who have supported the survey or the census operations financially and technically, however, it has been realized that there should be a procedure for accessing the raw data to all users through a legal basis;
- Whereas, the demand for raw data has recently increased and to entertain this demand to be made by the researchers and other data users who request for the raw data or for additional cross classification of variables, it is also realized that there is a need for cost sharing approach;
- Whereas, in order to entertain these users who request for raw data or detailed data that has not been published, there is a need for a clear procedure; and
- Whereas, to make the necessary arrangements to access the survey or the census reports not only through publications (hard copy) but also through electronic media such as diskettes, CD-ROM, …etc.;

Now therefore, in accordance with article 303/1972 of the proclamation provided to define the powers and the duties of the Central Statistical Office, this procedure for accessing the raw data has been issued.

1. SHORT TITLE

This Directive may be cited as the "Directive to Establish Procedures for Accessing Raw Data to Users"

2. DEFINITION

In this directive unless the context otherwise requires:

2.1 'Raw Data' shall mean a mass of numerical facts pertaining to households or establishments, collected by counting or measuring; coded or not coded, processed or unprocessed, at enumeration area, Kebele, Woreda, Zone, Region or Country level;

2.2 'Authority' shall mean the Central Statistical Authority;

2.3 'Census' shall mean a complete enumeration of units in a well defined territory at specified time which includes: population, housing, agriculture, industry, trade, and other similar sectors;

2.4 'Sample Survey' shall mean a method of data collection in which a representative portion of the population, household, dwelling, holding, or establishment, ...etc., selected from the total units. Then, data pertaining to social, housing, agriculture, industry, trade, household budget and prices, ...etc. are collected, compiled, processed, evaluated and the resulting data are published and disseminated;

2.5 'Administrative Record' shall mean the statistical data collected and compiled from records that are by-products of the day-to-day administrative exercises of government and non-government agencies;

2.6 'Country level raw data' shall mean raw data collected from Urban and/or Rural areas at country level;

2.7 'The budget prepared for the study' shall mean the capital budget allotted to collect and process the data for a specific census or survey;

2.8 'The lowest reporting level' shall mean the lowest administrative hierarchy at which the data from the study is processed and the result is released (this include: Kebele, Woreda, Zone or Region);

2.9 'Limited Variables' shall mean a part or some of the different variables (data) collected in the processes of conducting a census or a survey;

2.10 'A form for Requesting Access to the Raw Data': This is a form to be filled out by those who request for accessing the raw data and it indicates the type, reason for requesting and procedures for utilizing the raw data; and the rights and obligations of the users in utilizing the raw data; and

2.11 'Kebele' is the lowest administrative hierarchy with-in a wereda/district in the country.

## CHAPTER TWO
## ACCESSING THE RAW DATA

3. Conditions for Accessing the Raw Data

3.1 The Authority can access to users only the primary data that it has generated from censuses or surveys that it has carried-out. Censuses and Surveys include data generated through:

3.1.1 Household census or survey approach, and

3.1.2 Establishment census or survey approach;

3.2 Raw data are accessed to users only without possible identification of individuals, households or establishments:

3.3 Raw data are accessed to users only after the Authority has processed, analyzed, and published and disseminated the data generated through censuses and surveys;

3.4 Though the procedure indicated in 3.2 above is valid, however raw data can be also accessed, before the publication of the results, to those agencies (donors) who have supported the census or the survey financially or technically, particularly if these agencies participate in the preparation of the report;

3.5 Concerning the raw data generated through the censuses, users can have access to no more than 1-10 percent of the total data; and

3.6 Though the procedure indicated in 3.4 is valid, however if the users request the raw data at Kebele level, it is possible to let them have access to all the data at Kebele level.

## 4. AGENCIES HAVING ACCESS TO RAW DATA FREE OF CHARGE

4.1 Policy making Government Institutions/Organizations;

4.2 Students of higher education institutions who request access to raw data to fulfill their first or above degrees in various areas;

4.3 Those Organizations/Institutions that have financially and technically supported the operation of the survey/census from which the raw data has been generated;

5. AGENCIES OR PERSONS NOT ENTITLED TO HAVE ACCESS TO RAW DATA

5.1 Those who are not willing to fulfill the prescribed procedures in utilizing the raw data indicated in the "Form for Requesting Access to the Raw Data";

5.2 If there is a prior information that the agency/person requesting access to raw data could use it un-ethically or un- professionally;

5.3 If the Authority decided not to provide the raw data due to the size of the survey/census data or if the type of survey data requires special consideration;

6. OBLIGATIONS OF ORGANIZATION/PERSON REQUESTING ACCESS TO RAW DATA

6.1 The organization/person requesting access to the raw data should submit a brief written proposal that shows how the data will be utilized and for what purpose;

6.2 The organization/person requesting access to the raw data should not summarize and produce any information below the intended reporting level other than indicated in the survey design;

6.3 The organization/person requesting access to the raw data should not transfer the raw data it obtained with or without fee to third party;

6.4 The organization/person requesting access to the raw data should not use the data it obtained with possible identification of individuals or households or establishments;

6.5 The students of higher education institutions and researchers who are allowed to have access to the raw data without charge are obligated to provide a copy of their report presenting the analysis of the data;

7. PROCEDURES FOR ACCESSING RAW DATA TO USERS

7.1 The Data Processing Department of the CSA shall make the necessary preparatory arrangements to access raw data supplemented with the data dictionary as well as other essential information.

7.2 The Raw Data shall be accessed through the CSA's Public Relation Services after the necessary protocols are fulfilled, that is after filling-in the "Form for Requesting Access to Raw Data" and is authorized. Then, the Form shall be submitted to the Data Processing Department.

7.3 Except those organization/person who access raw data free of charge, others will be charged a certain fee that is levied by the Councils of Ministers of the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia.

8. AMOUNT TO BE CHARGED FOR RAW DATA

8.1 The amount to be charged for accessing the raw data of specific survey/census shall be on the basis of the decisions made on 23 April 2004 by the Council of Ministers as indicated in the table below.

8.2 For an organization/person requesting raw data at Regional, Zonal and Wereda level, the total fee for more than one lower reporting level shall be obtained by multiplying the amount to be charged for one reporting level with that of the total reporting levels requested.

| Sr. No | Budget for the Survey/Census | Amount to be charged including Diskettes |
|---|---|---|
| | **8.3 Country Level** | |
| a | Below 5 million Birr | 7,550 Birr |
| b | 5 million Birr and above | 15,100 Birr |
| | **8.4 One Reporting Level or Limited Variables** | |
| a | Below 5 million Birr | 550 Birr |
| b | 5 million Birr and above | 1,100 Birr |

8.5 The amount to be charged for an organization/person requesting published data with electronic media.

8.5.1 For publications with up to 100 pages, Birr 40,

8.5.2 For publications between 101-400 pages, Birr 80 and

8.5.3 For publications above 400 pages, 100 Birr will be charged.

9. AMENDMENT OF THE DIRECTIVE

The Central Statistical Authority based on its studies and evaluations shall amend this directive in due course.

10. EFFECTIVE DATE

This directive shall come into force beginning from the 9th of May 2004.

# CENTRAL STATISTICAL AUTHORITY

## FORM FOR REQUESTING ACCESS TO RAW DATA

1. Name of organization/person requesting the raw data:- ______________________

______________________

2. Requesting Organization/Person: -

- [ ] Governmental Office
- [ ] Research Institution
- [ ] Higher Education Institution
- [ ] Researcher
- [ ] University Student
- [ ] An Org. who contributed for the specific survey/census
- [ ] Private /Consultant Organization
- [ ] NGO
- [ ] International /Foreign Organization
- [ ] Other /specify/ ______________________

3. Year of undertaking and the name of the Census or Sample survey from which the raw data are being requested: - ______________________

______________________

4. The raw data is requested at: -

- [ ] Country level
- [ ] Regional level
- [ ] Zonal level
- [ ] Wereda level
- [ ] Kebele level
- [ ] Other /specify/ ______________________

5. For what purpose do you need the raw data? /please describe in short your proposal/

______________________________________________

______________________________________________

________________

6. Comments; the name and the signature of the head of the department from which access to raw data is requested: -

______________________________________________

______________________________________________

Name ________________ Signature ____________

7. Authorized person; please make access to raw data: -

☐ Free of charge

☐ With charge

Signature ____________________

8. If it's with charge, specify the total budget allocated for the census/survey /in Birr/ ______________________________

9. Head, Public Relations Service; if it's with charge the total amount to be paid /in Birr/ __________________________

Signature ____________________

10. Date/Month/Year/ ______________________

11. Obligations of organization/person requesting to access raw data

11.1 The organization/person requesting to access raw data shall not transfer the raw data it obtained with or without charge to third party;

11.2 The organization/person requesting to access raw data shall not use the data it obtained with possible identification of individual return or part thereof;

11.3 The researchers and students of higher educational institutions, who are allowed to have access to raw data without charge are obliged to give the copy of their report presenting the analysis of the data;

11.4 The organization/person requesting to access raw data shall not process the raw data below the lowest reporting level;

11.5 I the under signed organization/person agreed to obey the rules and regulations set from article 11.1-11.4. If failed to follow these obligations, shall be liable to the penalty provided under the appropriate article of the civil code issued in 1956 and order No. 79 of 1972 and proclamation No. 303 of 1972 to establish and define the powers of the Central Statistical Authority.

12. Witnesses names and signatures: -

12.1 ______________________ ____________ __________

12.2 ______________________ ____________ __________

12.3 ______________________ ____________ __________

13. Name of the Requesting Organization/Person ______________________________

Signature ________________

Date ________________